VOTE 2024

# የምርጫ ዳኛ ይሁኑ

የምርጫ ዳኛዎች፣ በአካባቢው የምርጫ ጣብያዎች የሚከፈሉ ግዜያዊ ሰራተኞች ሲሆኑ በምርጫ ጣብያ ውስጥ ምርጫን በተመለከተ ስለሚያስፈልግ ሁሉ የሰለጠኑ ናቸው። እንደ ምርጫ ዳኛ ሁኖ ማገልገል ለምርጫ ለመማር ዕድል የሚሰጥና ለማህበረሰቡ ትልቅ አገልግሎት የሚሰጥ ነው።

## እንዴት አድርጎ ማመልከት እንደሚቻል

የበለጠ ለማወቅ ከአከባቢዎ የከተማ ወይም የአውራጃ የምርጫ ጣብያ ጋር ይገናኙ። **እንዴት የምርጫ ዳኛ መሆን እንደሚቻል** የሚለውን በmnvotes.gov የሚገኘውን ዌብፔጅ (webpage) በመጎብኘትም አንዳንድ የምርጫ ማመልከቻ ሂደቶችንና ስለጉዳዩ ተጨማሪ መረጃን ያግኙ። ምርጫ በሚካሄድበት ዓመትም፣ ከግንቦት (May) 1 ቀን በፊት የፖለቲካ ፓርቲዎ ጋር ይገናኙ። ያሉበት ቦታ በ ዌብፔጁ ያልተመዘገበ ከሆነ፣ የምርጫ ዳኛ ለመሆን መሙላት የሚያስፈልገውን ፎርሙን ሞልተው ለአውራጃዎ የምርጫ ጽህፈት ቤት ኢሜል ያድረጉ።

## ማነው ማመልከት የሚገባው

በሚኖሶታ ውስጥ ለመምረጥ ብቁ የሆነ ሰው፣ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ማንበብ፣ መጻፍና መናገር የሚችል ሰው መሆን አለቦት።

አንዳንድ ገደቦች አሉ፡

- በአንድ ግዜ፣ በአንድ የምርጫ ቦታ ላይ ዘመዶች ( ባለቤት፣ ወላጅ፣ እንጀራ አባት፣ ልጅ፣ እንጀራ ልጅ፣ ወይም ወንድምና እህት) ሊያገለግሉ አይችሉም።
- የዕጩዎች ዘመዶች፣ እና ከዕጩው ጋር አንድ ቤት የሚኖር ሰው፣ ዕጩው እንደ ዕጩ በቀረበበት የምርጫ ጣብያ ሊያገለግሉ አይችሉም።
- ዕጩዎች በምርጫው ውስጥ ባሉበት ቦታ ሊያገለግሉ አይችሉም።

## የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪ ሰልጣኞች

የ16 እና የ17 ዓመት ዕድሜ ተማሪዎች እንደ ሰልጣኝ የምርጫ ዳኛ ሊሰሩ፣ ደሞዝ ሊከፈላቸውና ለስራ መግብያቸው የሚሆን ትልቅ ተመክሮ ሊቀስሙ ይችላሉ።

- ከምሽቱ 10:00 በኋላ አምሽተው እንዲሰሩ አትጠየቁም።
- ልክ እንደሌሎቹ ዳኞች አንድ ዓይነት ስራ እንድትሰሩ ይመደባሉ። ከፓርቲ ጋር የተያያዘ ስራ እንድትሰሩ ግን አይፈቀድም።
- ሌሎች ዳኞች የሚወስዱትን የስልጠና ትምህርት እንድትወስዱና እንድታጠናቅቁ ይጠየቃሉ።

ብቁ ሆኖ ለመገኘት፣ ከምርጫው ቀን በፊት ዕድሜዎ 16 ወይም 17 ዓመት መሆን አለበት፣ በሚኖሶታ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ወስጥ ወይም በቤት ውስጥ በሚሰጥ ትምህርት ጥሩ ውጤት የምታመጡ፣ የወላጆችዎና የት/ቤትዎ ፈቃድ ያሎት የአሜሪካ ዜጋ መሆን አለቦት፣

## ክፍያ

በበኑ ፈቃድ ያለ ክፍያ በነጻ ለመስራት ወይም እየተከፈሎት ለመስራት መመረጥ ይችላሉ። የሚከፈለው ገንዘብ በቦታና በተመክሮ ላይ የተመረኮዘ ነው። የተማሪ ሰልጣኞች፣ ዝቅተኛ ደሞዝ ከሚባለው ከሁለት ሶስተኛ ያላነሰ መከፈል አለባቸው።

## የስራ ቦታና ቃል የሰጡበት የግዜ

ቦታ: ከ18 ዓመት ዕድሜ በላይ የሆኑ አዋቂዎች፣ ማጓጓዥያው የሚጠይቀውን ሁሉ ማሟላት ከቻሉ፣ በመላው ሚኖሶታ የምርጫ ዳኛ በመሆን ማገልገል ይችላሉ።ሰልጣኞች በሚቀመጡበት በራሳቸው አውራጃና በአካባቢው ቦታዎች ማገልገል ይችላሉ።

ስልጠና፡ በግምት ወደ ሁለት ሰዓት የሚሆን የስልጠና ትምህርት መውሰድ ያስፈልጋል። አብዛኛዎቹ የትምህርት ግዜያት ምሽት ላይ ናቸው።

የስራ ቀናት፡ የመጀመርያውና አጠቃላይ ምርጫዎች የሚደረጉት በስራ ሰዓታት ውስጥ ነው። የመጀመርያውን ምርጫ ለማካሄድ ብዙ የሰው ሃይል አያስፈልግም። በህዳር ወር (November) በሚካሄደው በአጠቃላዩ ምርጫ ወቅት ብቻ ለማገልገል ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ።

የስራ ቀን የግዜ ሰሌዳ፡ በምርጫ ቀን የተለመደው የግዜ ሰሌዳ ከጥዋቱ 6:00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 9:00 ሰዓት አካባቢ ነው። በአንዳንድ ጉዳዮች፣ ግማሽ ቀን ብቻ ለመስራት ሊጠይቁ ይችላሉ።

## ከስራ ፈቃድ ማግኘት

አሰሪዎ፣ የምርጫ ዳኛ ሆኖ ለመስራት ምንም ደሞዝ የማይቆረጥበት የስራ ፈቃድ ሊሰጦት ይገባል። ለዚህ ብቁ ለመሆን የሚከተለውን ያድርጉ፡

- ከምርጫው ዕለት ቢያንስ ከ 20 ቀናት በፊት አሰሪዎን በጽሁፍ ማሳወቅ አለቦት።
- በጽሁፍ ካቀረቡት ጥያቄ ጋር አያይዘው የስራ ግዜዎን ሰሌዳንና የሚከፈሉትን መጠን አያይዘው ያስገቡ።

የእረፍት ቀናት ብለው በራስዎ ፈቃድ እረፍት መውሰድም ይችላሉ፣ ዳኛ በመሆንዎ የሚሰጦትን ደሞዝ እንደተጨማሪ ገቢ ሊወስዱት ይችላሉ። አለቃዎ የሆነ ዓይነት የእረፍት ግዜ ወይም የሆነ ዓይነት የሚከፈልበት የእረፍት ግዜ እንድትወስዱ ሊያስገድዶት አይችልም።

## የ2024 የምርጫ ቀናት

**ቀደም ብሎ የሚመረጥበት ግዜ:** ከጥር (January) 19 እስከ መጋቢት (March) 4 ቀን
**የፕሬዚደንትነት የመጀመርያው ምርጫ:** ማክሰኞ (Tuesday) መጋቢት (March) 5 ቀን

**ቀደም ብሎ ድምጽ መስጠት:** ከሰኔ (June) 28 እስከ ነሃሴ (August) 12 ቀን
**የመጀመርያ ደረጃ ምርጫ (PRIMARY ELECTION):** ማክሰኞ፣ ነሃሴ (August) 13 ቀን

**ቀደም ብሎ ድምጽ መስጠት:** መስከረም (September) 20 እስከ ህዳር (November) 4 ቀን
**የምርጫ ዕለት:** ማክሰኞ ህዳር (November) 5 ቀን

ለተጨማሪ መረጃ ይህንን ኮድ በመቃኘት **mnvotes.gov** ይጎብኙ